Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

# በፓራግራፍ 8 ተ.ቁ. 4 (DeuFöV) ሙያ ተኮር የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ደንብ መሠረት በትምህርት ሰጪ አካልና በተማሪዎች መካከል የሚደረግ የዉል ስምምነት

ለቋንቋ አጠቃቀም ቅለት ተብሎ በዚህ ዉል ስምምነት ዉስጥ ወንዴ ጾታ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን መታወቅ ያለበት ግን የወንዴንም ሆነ የሴቴንም ጾታዎች በእኩልነት የሚገልጽ መሆኑን ነዉ።

በ

| |
|---|
| የተማሪዉ አባት ሥም፣ መጠሪያ ሥም፣ የልደት ቀን፣ |

**እና**

| |
|---|
| የትምህት ቤቱ ስም እና አድራሻ |

## የሚከተለዉ ዉል ሥምምነት ተፈጽሞአል፥

## 1. <u>ክፍያን በተመለከተ</u>

ሙያ ተኮር የቋንቋ ትምህርት በመሠረቱ ከክፊያ ነጻ ነው።

ይህ የማይመለከታቸዉ ደግሞ ሥራ ያላቸዉና በዚህም የተነሣ በማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር ሁለት (SGB II)፣ ማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር አስራሁለት (SGB XII) ወይም ለስደተኞች ስለሚሰጥ የኖሮ መደጎሚያ ሕግ መሠረት (AsylbLG) ለመኖር ከመንግስት እርዳታ የማያገኙ ከሆነ፣ ወይም የሥራ አጥነት ገንዘብ የማይገባቸው፥ በተጨማሪ በፓራግራፍ 57 ተ.ቁ. 1 ማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር ሦስት (SGB III) መሠረት በሙያ ሥልጠና ላይ ካልሆኑ፣ የዓመት ገቢዉ ለብቻ ከሆነ ከ20,000 € እንዲሁም ከትዳር አጋር ጋር ከ40,000 € በላይ የሚበልጥ ከሆነ ከክፊያ ነጻ ሊሆኑ አይችሉም። እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ለትምህርቱ ገንዘብ መክፈል አለባቸዉ። ትምህርት የሚሰጠዉ አካል በምዝገባ ግዜ ለትምህርቱ ተካፋዮች ክፊያን በተመለከተ ማሳወቅ አለበት። አንድ ተማሪ ለትምርቱ ወይም ለኮርሱ የሚያስፈልገዉን ጠቅላላ ገንዘብ ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት ሙሉ በሙሉ መከፈል አለበት።

ሥራ ኖሮአቸዉ በሚያገኙት አነስተኛ ገቢ ምክንያት ትምህርቱን በነጻ የሚማሩ ከሆነና በራሳቸዉ ምክንያት ሙያ ተኮር ትምህርቱን የሚያቋርጡ ከሆነ ለትምህርት የሚከፈለዉን ገንዘብ መክፈል አለባቸዉ። ነገር ግን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ትምህርቱን ቢያቋርጡ ማስረጃዉን ለፌደራል የስደተኞች እና የጥገኝነት ጠያቂዎች መሥሪያ ቤት (BAMF) ማቅረብ አለባቸዉ።

የመማሪያ መጽሐፍት ለትምህርቱ ተሳታፊዎች ከትምህርት ሰጪዉ አካል በነጻ ይሰጣሉ።

## 2. የመጓጓዣ ወጪ

የትምህርቱ ተካፋይ የሆኑ፣

- በማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር ሦስት  (SGB III) መሠረት የስራ አጥ ገንዘብ I ድጋፍ የሚያገኙ፣
- በማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር ሁለት (SGB II) መሠረት የስራ አጥ ገንዘብ II ድጋፍ የሚያገኙ፣
- በማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር አስራሁለት (SGB XII) መሠረት ለመኖር የመንግስት እርዳታ የሚሰጣቸው፣
- በማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር ሦስት (SGB VIII)፣ ለስደተኞች ከሚሰጠዉ እርዳታ ፈንታ ለወጣቶች የሚሰጥ ድጋፍ የሚያገኙ፣
- ለስደተኞች ስለሚሰጥ የኖሮ መደጎሚያ ሕግ መሠረት (AsylbLG) የስደተኛ እርዳታ የሚያገኙ፣
- በማህበራዊ ሕገ ደንብ ቁጥር ሦስት (§ 56 SGB III) ለሙያ ትምህርት ድጋፍ የሚሰጣቸው፣

ለመጓጓዣ ኣገልግሎት የሚያስፈልግ ጥቅል ድጋፍ ሊሰጥዎት ይቻላል። የሚሰጠውን ድጋፍ ትምህርት በሚሰጥበት ግዜ ከተቋረጠ፡ ይህንን ጉዳይ በስልጠናው የሚሳተፍ ሰው ወድያው ለትምህርት ሰጪ አካልና ለፌደራል መሥሪያ ቤት ማስረጃ መስጠት ይገባል።

ለመጓጓዣ የሚሰጥ ጥቅል ድጋፍ ሊሰጥዎት የሚችለዉ ትምህርት የሚሰጥበት ቦታ ከመኖሪያ ቤታቸዉ በእግር ከ 3 ኪ.ሜትር በላይ ከራቀ ነዉ። የመጓጓዣ ድጋፍ ማመልከቻ ለትምህርት ሰጪዉ አካል መቅረብ አለበት። በዚህ ምክንያት ለመጓጓዣ የሚሰጥ ጥቅል ድጋፍ ጥያቄዎ ተቀባይነት ካላገኘ እርስዎ ዉሳኔዉን በመቃወም ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ወይም ለትምህርትር ሰጪ አካል ዉክልና ሰጥተዉ እንዲያስፈጽምልዎ ማድረግ ይችላሉ።

ለመጓጓዣ የሚሰጥ ጥቅል ድጋፍ ጥያቄዎ ከፌደራል የስደተኞች እና የጥገኝነት ጠያቂዎች መሥሪያ ቤት (BaMF) አዎንታዊ መልስ ካገኘ ይህ ዉሳኔ ጠቅላላ የትምህርት ግዜ እስኪያልቅ ድረስ ያገለግላል። የመጓጓዣ ዋጋ ላይ ጭማር ቢደረግ ዉሳኔዉ አይቀዬርም። የመኖሪያ አድራሻዎን ከቀየሩ የተሰጠዉ ዉሳኔ ዋጋ የለዉም። አስፈላጊ ከሆነ ሌላ አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ አለብዎት።.

## 3. የህጻናት ማቆያን በሚመለከት

ህጻናት ልጆች ላሉአቸዉ ተማሪዎች ትምህርት ሰጭው አካል የመዋእለ ህጻናት በማፈላለግ ረገድ ይተባበራል።

## 4. ኮርሱ የሚጀሚረበት ጊዜ

አንድ ተማሪ ለትምህርት ከተመዘገበ በአራት ሣምንት ግዜ ዉስጥ ሙያ ተኮር ትምህርቱ መጀመር ይኖርበታል። ትምህርቱን በዚህ ግዜ ዉስጥ የማይጀምር ከሆነ ትምህርት ሰጪዉ አካል ተማሪዉን ተመሣሣይ ትምህርት ወደሚሰጥ ትምህርት ቤት መላክ አለበት። ትምህርት ቤቱ ለተማሪዉን ትምህርት የመካፈል ፍቃዱን ዋናዉን ፍቃድ መልሶ ይሠጠዋል። ለፌደራል ቢሮ ተማሪዉን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የላከ መሆኑን ያሳዉቃል።

አንድ ተማሪ የአድራሻ ለዉጥ ካደረገ ለዉጡን ለትምህርት ሰጪዉ አካል በፍጥነት ማሳወቅ አለበት። ከአንድ የትምህርት ሰጪ አካል ወደ ሌላ መለወጥ የሚቻለዉ ከባድ ችግር ሲገጥም ብቻ ነዉ። አንድን ሰዉ ከባድ ችግር ገጠመዉ የሚባለዉ ደግሞ ትምህርት ሰጪዉ አካል አድራሻዉን ቀይሮ ተማሪዉ አዲሱ አድራሻ ድረስ ለመሄድ የሚወስድበት ግዜ ከ 90 ደቂቃ በላይ የሚወስድበት ከሆነ ነዉ። ይህ በሚሆንበት ግዜ የትምህርት ሰጪ አካል ለዉጥ ጥያቄ ተማሪዉ ለሚመለከተዉ የፌደራል ቢሮ ማመልከት አለበት።

ተማሪው ትምህርቱን በትምህርት ሰጭው አካል ምክንያት ካቋረጠ ትምህርት ሰጭው አካል ተማሪውን ወደሌላ ትምህርት ቤት ማስተላልፍ ይኖርብታል።

## 5. በትምህርት ወቅት ከተማሪው የሚጠበቁ ምግባሮች

ተማሪዉ ትምህርቱን በየቀኑ በተከታታይነት ተገኝቶ መማር አለበት። ተማሪዉ ትምህርቱ በሚሰጥበት ግዜ በንቃት ተሳታፊ የሚሆን መሆኑን ይገልጻል። የትምህርት ሰጪውን አካል የቤት መተዳደሪያ ህግ እና ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት።

የትምህርት ሰጪው አካል የቤት መተዳደሪያ ህግ እና ድንጋጌዎችን መጣስ ትምህርቱን እስከማቋረጥ ሊያደርስ ይችላል።

## 6. ከትምህርቱ ላይ ስለመቅረት

ትምህርቱ በሚሰጥባቸዉ ጊዜዓቶች በግል ደረጃ የታቀደ ዓመታዊ ፍቃድ መሄድ አይቻልም።

ትምህርቱን የሚያቋርጡ ተማሩዎች ወይም የኮርሱ ተካፋዮች ካሉ ትምህርት ሰጪዉ አካል ለፌደራል የስደተኞች እና የጥገኝነት ጠያቂዎች መሥሪያ ቤት ወይም ትምህርቱ ላይ እንዲካፈል ለፈቀደዉ መሥሪያ ቤት በፍጥነት ያሳዉቃል። ከዚህም ሌላ አንድ ተማሪ በኮርሱ ላይ እንዲካፈል ከጆብ ሴንቴር የተላከ ከሆነና ከትምህርቱ ላይ ብዙ ግዜ ቀርቶ ኮርሱን ወይም ትምህርቱን በዉጤት መጨረሱ አደጋ ላይ ከወደቀ ትምህርት ሰጪዉ አካል በሙያ ተኮር የቋንቋ አሰጣጥ ደንብ በ § 9 ተ.ቁ. 5፣ 2 ዓረፍተ ነገር (i.V.m. §9 Abs.5 Satz 2 DeuFöV) ሳይዘገይ ለጆብ ሴንቴር ማቅረብ ያሳዉቃል።

የትምህርቱ ተሳታፊዎች ትምህርት በሚቀሩባቸው ግዜዎች ትምህርት ቤቱን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸዉ፣ ይህም በተለይም የሚሆነዉ አንድ ተማሪ፥

- ትምህርቱ በሚጀምርበት ቀን ያለምንም በቂ ምክንያት ከቀረ
- በማስረጃም ሆነ ያለማስረጃ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ከትምህርቱ ላይ ሲቀር
- ከ20 ፐርሰንት (20 %) በላይ ከጠቅላላዉ የትምህርት ክፍለ ግዜዓቶች ከትምህርቱ ላይ ከቀረ

አንድ ተማሪ 30 ፐርሰንት (30 %) ያህል ሙያ ተኮር ከሆነ የቋንቋ ትምህርት ላይ ከቀረ ዉጤታማ በሆነ ሁኔታ ኮርሱን ይጨርሳል ተብሎ አይጠበቅም። ይህ በሚሆንበት ግዜ ትምህርት ቤቱ ተማሪዉ ትምህርቱን ያቋረጠ መሆኑን ለሥራ ኤጀንሲ፣ ወይም ለሥራ ማዕከል ወይም ለፌደራል ቢሮ ማሳወቅ አለበት።

አንድ ተማሪ ከትምህርቱ ላይ ከቀረ ለቀረበት ምክንያት ማስረጃ ማቅረብ አለበት። እንደዚህ ዓይነት ማስረጃ ለምሳሌ የሐኪም ወረቀት ለትምህርት ቤቱ በፍጥነት መሰጠት አለበት። አንድ ተማሪ ከኮርሱ ላይ በሚከተሉት ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች ሊቀር ይችላል፣

| | |
|---|---|
| በህመም | **እስከ አንድ የትምህርት ቀን፣** ተማሪዉ ለትምህርት ሰጪዉ አካል በጽሁፍ ወይም በቃል ሕመሙ የጀመረበትን ጊዜ ማሳወቅ ይኖርበታል። (ከዚህም ሌላ ትምህርት ሰጪዉ አካል የጽሑፍ መግለጫ ያደርጋል)<br>**ከሁለተኛዉ ቀን ጀምሮ** የሃኪም ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። |

| | |
|---|---|
| አንድ እድሜዉ ከ 12 ዓመት ያላለፈ ታማሚ ሕጻን ልጅ የሚንከባከብ ሰዉ፣ ልጁን የሚጠብቅ ሌላ ሰዉ ካልተገኘ | የሕጻኑን መጠበቅ አስፈላጊነት ሐኪም ካረጋገጠ ኮርሱ ከሚጀመርበት የመጀመሪያዉ ቀን አንስቶ ይሠራል |
| ባልተገመተ ምክንያት እድሜዉ ከ 8 ዓመት ያላለፈ ሕጻንን የሚጠብቅ ሰዉ፣ ለምሣሌ በሕመም ምክንያት ልጁን መጠበቅ ካልቻለ | ሕጻኑን የሚጠብቁት /ለምሣሌ መዋዕለ ሕጻናት/ ማስረጃ ከሰጠ |
| የተከሰተው የህጻናት ማእከሉ ወይም የትምህርት ቤቱ መስተጓጎል እና መዝጋት በባለ ስልጣኖች ወይም የመንግስት አስተዳደሮች ምክንያት ከሆነና ፡ ህጻናቶቹ ዕድሜያቸው 12 ዓመት ያልደረሱ ከሆኑ | ስለ መዝጋቱ የሚመለከት ተጨባጭ የማረጋገጫ ምስክርነት በሚላክበት ግዜ (የማያስፈልግ የመዝጋት መመሪያዎች በ ኣገር ወይም ክልል ወይም የከተማ ኣሰተዳደሮች ተቀባይነት ያለው) |
| ተማሪዉ ወይም የኮርሱ ተካፋይ በሚኖርበት ቤት ዉስጥ የሚኖር ሕጻን ልጅ የሚንከባከቡ ከሆነ | የቤቴሰቡን አባል ወይም የዘመዱን መጠበቅ አስፈላጊነት ሐኪም ካረጋገጠ |
| በጋብቻ ምክንያት | **ሁለት የትምህርት ቀናቶች፣** ሆኖም ግን ማስረጃ ማቅረብ አለበት /የጋብቻ ሰርተፊኬት/ |
| የአራሥነት ግዜ ላይ ከሆነ/ከሆነች | ማስረጃ ማቅረብ ካቀረበ /የሐኪም ማስረጃ/ |
| የተማሪዉ የትዳር ጓደኛ / ወይም ፍቅረኛ ልጅ ከወለደች | **ሁለት የትምህርት ቀናቶች**፣ ሆኖም ግን ማስረጃ ማቅረብ አለበት /የሐኪም ማረጋገጫ. የልደት ሰርተፊኬት/ |
| የትዳር አጋር በሕይወት ካለፈ/ሕጻን ልጅ ወይመ ከወላጆች አንዱ ከሞተ | **እስከ ሁለት የትምህርት ቀናቶች**፣ ማስረጃ ካቀረበ<br>**እስከ አምስት የትምህርት ቀናቶች**፣ የሟቹ የቤተሰብ አባል በዉጭ አገር ቀብሩ የሚፈጸም ከሆነ |
| በቀጠሮ ምክንያት ለምሣሌ የዋጭ ዜጎች ቢሮ / ፍርድ ቤት | ተገቢ የሆነ ማስረጃ ከቀረበ |
| ትምህርቱን እንዲማር የፈቀደዉ መሥሪያ ቤት ከትምህርት እንዲቀር ፍቃድ ከሰጠ | ተገቢ የሆነ ማስረጃ ከቀረበ |
| በሥራ ላይና በሥልጠና ላይ ላሉት የሚሠሩብት መሥሪያ ቤት የዓመት ፍቃድ ከሠጣቸዉ | ፍቃዱ የተሰጠበት ወረቀት ቅጂ ወይም ኮፒ |
| ብቤት የመቆየት ታዛዝ ብክልል ባለስልጣኖች የተሰጠ | ስለ መዝጋቱ የሚመለከት ተጨባጭ የማረጋገጫ ምስክርነት በሚላክበት ግዜ (ኣስፈላጊ ካልሆነ የመኖርያ ኣድራሻ ትእዛዝ ብቁ መሆኑ ይታወቃል) |

| | |
|---|---|
| የኮቪድ-19 ወረርሽ በሽታ እንዳይኖራችሁ ራሳችሁን ለማወቅ ምርመራ ለማካሄድ | **ስለ መመርመርያ ቀንና ውጤታችሁን እስከምትቀበሉ ያሉ ቀኖች** የሚገልጹ ትክክለ መረጋገጫዎች ማቅረብ |
| ላ ኣደጋ ከተጋለጡ ቡድኖች ኣባል ከሆናችሁ ፡ ከህክምና ጋር ትስስር ካላቸው ፡ በህክምና መስፈርቶች የጸና ከ ኮቪድ-19 ተመሳሳይነት ያለው ምልክቶች ከታየባችሁ ፡ ወደ መማርያ ክፍል ለመግባት ኣይፈቀድላችሁም። | ለ ኣደጋ ከተጋለጡ ቡድኖች ኣባል መሆናችሁ መረጋገጫ በምታቀርቡበት ግዜ ፡<br>ማብራርያ፡ ማረጋገጫው በምታቀርቡበት ግዜ በኣካል ስለመገኘት በፈቃዳችሁ የሚወሰን ነው። ይሄ ለኣደጋ ለተጋለጡ ቡድኖች የሚሰጥ መስፈርቶች ብታሟሉን ይሰራል። |

ትምህርት ቤቱ ወይም ትምህርት ሰጪዉ አካል ማንኛዉንም የሐኪምና ሌላ ማስረጃዎችን ለቀሩበት ማረጋገጫ ስለሆነ ያስቀምጣቸዋል።

## 7. የሰርቴፊኬት / የምሥክር ወረቀት ፈተናዎች

ትምህርት ቤቱ ለእያንዳንዱ ተሳታፊ/ተማሪ የሙያ ተኮር የቋንቋ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ያቀርባል። እንደ ንግድ ወይም ድርጅት እና ቲክኒካዉ ተኮር ለሆኑት ኮርሶች በሰርተፊኬትት ፈንታ በመማር ሂደቱ ላይ ስለተገኘው የእውቀት ደረጃ የተገለጸበት የተሳትፎ ወረቅት ይሰጣል። ፈተናውን ያላለፉ ተሳታፊዎች ፈተናውን በድጋሚ የመፈተን አንድ ተጨማሪ እድል አላቸው።

ትምህቱን ያላለፈው ተሳታፊ በድጋሚ ለመሳተፍ ጆብ ሰንተር ወይም አርባይትስ አጌንቱር ጋር ማመልከቻ በድጋሚ ማስገባት ይኖርበታል።

የሰርቴፊኬት ፈተናዉና በድጋምም የሚወሰደዉ የሰርቴፊኬት ፈተና ከክፍያ ነጻ ነው።

ለሁለተኛ ግዜ ፈተናውን ያላለፈ ተሳታፊ ወይም ተማሪ ከትምህርት ቤቱ የተሳትፎ እና የተማርውን የትምህርቱን እውቀት ደረጃን የሚገልጽ ማረጋገጫ ወረቀት ይሰጠዋል። ትምህርት ቤቱ የተሳትፎ ማረገጋጫ ወረቀቱን ቅጂ / ኮፒ ለፌደራል ቢሮ፣ ለጆብ ሴንተር እንዲሁም ለአርባይትስ አገንቱር ያስተላልፋል። ይህ በተመሣሣይ ሁኔታ ለሰርተፊኬት ፈተናዎችም ይሠራል።

## 8. ወሳኝ ኩኔቶች ምዝገባን በተመለከተ

የተማሪዎች ወይም የኮርሱ ተሳታፊ ኩኔቶች ወይም ስለግለሰቡ የሚገልጹ መረጃዎች፣ የወሳኝ ኩኔቶች ሕግ በሚለዉ መሠረት ኮርሱን በአግባቡ ለማስከድና የሙያ ተኮር የቋንቋ ትምህርት ክፊያዎችን ከሚመለከታቸዉ መሥሪያ ቤቶች ጋር /ለምሣሌ የፌደራል ቢሮ፣ አርባይትስ አገንቱር፣ የኑሮ ድጋፍ ሰጪ መሥሪያ ቤት/ ከሚደረግ መጻጻፍና ግልጋሎት ዉጪ ለሌል ጉዳይ አይዉሉም። በተለይም ለንግድ ጉዳዮች እነዚህን ኩኔቶ መጠቀም አይቻልም። ለሦስተኛ አካላትም አሳልፎ መስጠት አይቻልም።

ትምህርት ሰጪዉ አካል የተማሪ ኩኔቶችን ወይም ዳታዎችን ትምህርቱ ካለፈ ቢያንስ ከአምስት ዓመት በኋላ ማጥፋት አለበት።

ተማሪዉ ወይም የኮርሱ ተካፋይ የእሱን ፋይሎች / እሱን የሚመለከቱ ማስረጃዎችን/ የማዬት መብት አለዉ።

,

ቦታ, ቀን

______________________________

የተማሪዉ ወይም የኮርሱ ተካፋይ ፊሪማ
(እባክዎ ይገንዘቡ፡ ፊርማ ከሌለው፡ ለመሳተፍ የተፈቀዳቸ ተሳታፊዎቸ እዝህ መሳተፍ ኣይቻልም። እድሜዉ ከ 18 በታች ለሆነ የትምህርቱ ተካፋይ: የወላጆች ወይም በሕግ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ ፊሪማ ያስፈልጋል።)

______________________________

የትምህርት ቤቱ ፊሪማ